# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**መስከረም 20 ቀን 2004 ዓ.ም**

**የወያኔ ቡድን ቁጥራቸው የበዛ ባለስልጣናትን አሁንም አባረረ፤**

**በጡረታ የተሰናበቱ የህወሀት መኮንኖች ደግሞ ስራ እየተመደቡ መሆኑ ተጋለጠ፤**

**የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊና ግርማ ወ/ጊዮርጊስ የተላከላቸውን ደብዳቤ አንቀበልም አሉ፤**

የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ ቡድን አንዱን ከአንዱ እያመታታና እያመሰ የሚያደርገውን ጉዞ በመቀጠል በነባር አባላቱና በተለይ በአጋር በሚባሉት የወያኔ ተለጣፊ ድርጅቶች ውስጥ ከፍተኛ ትርምስ እንዲፈጠር እያደረገ መሆኑ ታወቀ::

በዚህም መሰረት በቤንሻንጉል ጉሙዝ የተጀመረው ትርምስ እና ምንጠራ በመቀጠል 35 ባለስልጣናት ሲባረሩ በምትካቸው በአዲስ አበባ ሲቪል ሰርቪስ እና በሌሎች ተቋዋማት ውስጥ የፖለቲካ ኮርስ ሲሰጣቸው የነበሩ ሳይጠሩዋቸው አቤት ሳይልኩዋቸው ወዴት የሚሉትን እየሰገሰጉ እንደሚገኙም ታውቆዋል::

በክልሉ ምክትል ፕሬዝዳንት ላይ የተጀመረው ምንጠራ እስከ ቢሮ ኃላፊዎች እና የክልሉ የፖሊስ አዛዥ እና የማረሚያ ቤት አስተዳደር ኮሚሽነር እንዲሁም የተለያዩ የክልሉ ኃላፊዎች ድረስ የደረሰ ምንጠራ የተደረገ ሲሆን በተለይ ከህዝብ ጋር ቀጥታ ግንኙነት አላቸው የሚባሉት ቁጥራቸው የበዛ የከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የወረዳ ፍርድ ቤት ደኞችም የዚሁ የምንጠራ ሰለባ እንደሆኑ ለማወቅ ተችሎዋል::

በቤንሻልጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ የተጀመረው ምንጠራም ወደ እስራት እየተቀየረ በመሆኑ ከአሶሳ ወደ አዲስ አበባ ማዕከላዊ ምርመራ እያመጡዋቸው መሆኑን የጠቀሰው የደረሰን ዘገባ በክልሉ

መታሰር ሲገባቸው ወደ ፌዴራል ማምጣታቸው በእነ መለስ ዜናዊ የተሰጠ የፖለቲካ ትዕዛዝ እንደሆነም ለማወቅ ተችሎዋል ሲል ዘገባው አመልክቶዋል::

አምና የተጀመረው የኦህዴድ ምንጠራ ዘንድሮም ተስፋፍቶ ውስጥ ውስጡን ከስራና ከስልጣን ማባረሩ እንደቀጠለ የጠቆመው የደረሰን ዘገባ በቅርቡ ቁጥራቸው የበዛ ዳኞችም ከስራ ሊባረሩ እንደቻለም ታውቆዋል::

በኦሮሚያ ክልል የኦህዴድ አባሎች የሆኑ 105 ነባር የከፍተኛ እና የወረዳ ዳኞች ከደረጃቸው ዝቅ የተደረጉ......ከነበሩበት ዞን የተዛወሩና ከስራቸው የተቀነሱ ሲሆን 35 ያህሉ የክስ መዝገብ ተዘጋጅቶባቸው በቅርቡ ለፍርድ እንደሚቀርቡም የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

ከነዚህ ውስጥ 15 የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች እና 5 የህግ ኦፊሰሮች ጭምር ሙሉ ለሙሉ ከስራቸው የተባረሩ ሲሆን በታገዱትም ሆነ በተባረሩት ምትክ እውቀት እና ችሎታ የሌላቸው በማስተማር ስራ ላይ የነበሩ የኦህዴድ ካድሬዎች በክረምት ወራት ውስጥ ለሁለት ወር ስልጠና ተሰጥቶዋቸው በየፍርድ ቤቱ በዳኝነት እንደተመደቡም የደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

የኦሮሞን ህዝብ አንገት አስደፍተው ለወያኔ እንዲያጎበድድ እያደረጉ ያሉት እነዚሁ እበላ ባይ ሆድ አደር የኦህዴድ ካድሬዎች ቀስ በቀስ የመለስን ክንድ እየቀመሱ የቀናቸው ከስራ ሲባረሩ ያልቀናቸው እየተከሰሱ ወደ ዘብጥያ እየወረዱ ነው ሲል የደረሰን ዘገባ ጨምሮ አስረድቶዋል::

በአዲስ አበባ የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን የሚባለው መስሪያ ቤት ሰራተኞችም ለሁለት ተከታታይ ሳምንታት በተደረገ ምንጠራ 150 የጥበቃ ፖሊሶች.....15 ከፍተኛ መኮንኖች እና ሌሎችንም ያካተተ ምንጠራ መደረጉ ታውቆዋል::

በተለይ 150 የጥበቃ ፖሊስ አባሎች ከስራ የታገዱት በእስር ላይ ካሉት የፖለቲካ እስረኞች ጋር ትሞዳሞዳላችሁ በሚል መሆኑን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦ እያንዳንዱን ከተለያዩ የፓለቲከ ድርጅቶች ጋር በማያያዝ መሆኑን የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

ነባር እና ከ30 ዓመት በላይ የሰሩ መኮንኖችን ደግሞ የፖሊሶቹ አስተባባሪ ናችሁ እያሉ እየፈረጁ በግምገማ የቂም ስቅላቸውን ሲያሳዩዋቸው የከረሙ ከመሆኑም በተጨማሪ ለግዜው የቂም አስረኛ ተደርገው እንዳሉም ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ በተደረገ የምንጠራ ዘመቻ እስረኛውን የቂም ስቅል የሚያሳዩትን ከበረሀ የመጡ የህወሀት ታጋዮች ግምገማው የማይመለከታቸው መሆኑን የጠቀሰው የደረሰን ዘገባ በተለይ ለአንድ አልጋ 20 ሺህ ብር ጉቦ እየተቀበሉ ገንዘብ የሌለው እስረኛ በብርድ እና በውርጭ እየተጠበሰ ባለበት እና ይህንንም ጉዳይ ከዝቅተኛ ሰራተኛ እስከ ከፍተኛ ባለስልጣን እያወቀ አንዳችም እርምጃ ሳይወሰድባቸው ምንም ውስጥ በሌሉበት እና ተሳትፎ ባላደረጉት ፖሊሶች ላይ ታፔላ እየለጠፉ ከማባረራቸው በተጨማሪ የቂም እስረኛ ማድረጋቸው አይን ያወጣ አድልኦ በየተቋዋሙ እየተስፋፋ በመምጣቱ ሁኔታው ወደፊት እጅግ ከባድ አደጋ ሊኖረው እንደሚችልም ስጋት እያሳደረ መምጣቱን ሰራተኞቹ ይገልፃሉ::

የመለስ ዜናዊ ቡድን በየሄደበት የፖለቲካ ኪሳራ በገጠመው ቁጥር የአሽባሪ ቡድኖች አባል፤ የሻዕቢያ ተላላኪ ወዘተ… እያለ ታፔላ ከመለጠፉም በላይ እያፈሰ ጨለማ እስር ቤት እያጎረና እያሰቃየ መሆኑን ሰሞኑን በሀገር ውስጥ እያደረገ ያለው ምንጠራ በቂ ማረጋገጫ መሆኑም ታውቆዋል።

በተመሳሳይ ብዙ አምራች እና አትራፊ የመንግስታዊ ተቁዋሞችን እየጠቀለለ ያለው በአዲስ መልክ በቅርቡ የተዋቀረው የወያኔ ንብረት የሆነው ኢንጂነሪንግ የተሰኘው መስሪያ ቤትም ነባር ሰራተኞችን በየምክንያቱ እያባረረ በጡረታ የተገለሉ የህወሀት ታጋዮችን እየሰገሰገ መሆኑም ታውቆዋል።

በቅርቡ ወደ መከላከያ ኢንጅነሪንግ ከተጠቃለሉት መንግስታዊ አምራች መስሪያ ቤት መሀከል ኢትዮ ፕላስቲክ የተሰኘው ስመ ጥር እና አትራፊ ድርጅት አንዱ ሲሆን ነባር የድርጅቱ ሰራተኞች በየሰበቡ እየተባረሩ የቀድሞ ታጋይ የወቅቱ መኮንኖች የሆኑ የህወሀት ሰዎች ቦታውን እየተቆጣጠሩት መሆኑ ታውቆዋል።

የኢትዮ ፕላስቲክ የአስተዳደር እና የሂሳብ ክፍል ኃላፊ የነበሩት ነባር ሰራተኞች ተባርረው በጡረታ ሲሰናበቱ የመከላከያ አባሎች ቦታውን እንዲቆጣጠሩ የተደረገ ሲሆን ተራ ሰራተኞችም እየተሰናበቱ ከሰራዊቱ ውስጥ እየተመለመሉ የመጡ አባሎች እየተመዱቡበት መሆኑን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

የመከላከያ ኢንጅነሪንግ የተሰኘው መስሪያ ቤት በአዲስ መልክ የተቁዋቁዋመ ሲሆን በስራ አስኪያጅነት የተመደበውም በሚኒስትር ማዕረግ የአድዋ ተወላጁ የህወሀት ታጋይ የሆነው ብ/ጄኔራል ክንፈ ዳኘው የተባለ መሆኑም ታውቆዋል።

በኦህዴድ አባሎች፤ በየአጋር ድርጅቶቹ እና በእስር ቤት ፖሊሶች የተጀመረውን ምንጠራ ተከትሎ በአዲስ አበባ በተለያዩ መስሪያ ቤት ውስጥ የሚሰሩ ነባር ሰራተኞችን የመመንጠሩ ዘመቻም ሊጀመር መሆኑ ከየመስሪያ ቤቱ ሾልኮ የወጣው ጥቆማ አጋለጠ።

የወያኔ ቡድን የደረሰበትን የውስጣዊ ፖለቲካ ክፍፍል ለመጠገን ሲል በየመስሪያ ቤቱ አስቸኩዋይ ስብሰባ እንዲጀመርና ምንጠራ እንዲደረግ ምስጢራዊ ትዕዘዝ መበተኑንም ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል።

በተሰጠው ትዕዘዝ መሰረት በሁሉም መስሪያ ቤት ውስጥ አጣዳፊ ግምገማ ተደርጎ የአምስት ዓመቱን የእድገት እና የትራንስፎርሜሽን እቅድ የማይቀበሉና ለተግባራዊነቱም ተሳትፎ የማያደርጉት የእድገት ማነቆዎች በመሆናቸው በአስቸኩዋይ እንዲባረሩ የሚል መመሪያ መተላለፉንም የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል።

በመጀመሪያ ይህንኑ ትዕዘዝ መተግበር ከጀመሩት መስሪያ ቤቶች ውስጥ የአዲስ አበባ የውልና ማስረጃ ቢሮ ሰራተኞች ግንባር ቀደሞች ሲሆኑ የስራ ቀናቸውን ዘግተው ቅዳሜ ሙሉ ቀን በዚሁ አስቸኩዋይ ስብሰባና ግምገማ ተጠምደው መዋላቸው ታውቆዋል።

የመንገድ ትራንስፖርት መስሪያ ቤት ሰራተኞችም በከፊል(በፈረቃ) ግምገማውን የጀመሩ ሲሆን አብዛኛዎቹ በተሰጣቸው የማስፈራሪያ እና የማስደንገጫ ቃላት በመበሳጨት ሲያጉረመርሙ እንደነበርም ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

በዚሁ በተጀመረው የአስቸኳዋይ ግምገማ ላይ ከስልጣናቸውና ከቦታቸው የሚነሱ እንዳሉ የጠቆመው የደረሰን ዘገባ እስከ ዛሬ ከስልጣናቸው ሲነሱ ወደ ዝቅተኛ ቦታ የሚመደቡ ሲሆን አዲሱ ምንጠራ ግን ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ተያይዞ ወደ ዘብጥያ ማውረድ መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

በየመስሪያ ቤቱ የተጀመረውን ግምገማ ተከትሎ የግል ትምህርት ቤት መምህራኖችም በትምህርት አሰጣጥ ችግሮች ዙሪያ ለመነጋገር በሚል ሰበብ ቅዳሜ መስከረም 13 ቀን 2004 ዓ.ም ቀኑን ሙሉ በስብሰባ ተወጥረው መዋላቸው ታውቆዋል፡፡

ምንም እንኳዋን በትምህርት አሰጣጥ ችግሮች ዙሪያ የሚል ስም ተሰጥቶት የነበረው የስብሰባ አጀንዳ ተቀይሮ መምህራኖች በየትምህርት ቤቱ ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው....... ተማሪዎች አመፅ ቢያነሱ ተጠያቂው መምህሩ እንደሆነ ......በየትምህርት ቤቱ መምህራኖች በምንም መልኩ ከክፍለ ከተማው ፍቃድ ሳያገኙ እንዳይሰበሰቡ......የተጀመረውን የህዳሴ ግድብ ከመደገፍ በስተቀር የተቃውሞ ሀሳብ መሰንዘር ወንጀል መሆኑን........እና ሌሎች የማስፈራሪያና የማስጠንቀቂያ ዛቻ ሲሰጣቸው የዋለ መሆኑ ተጠቁሞዋል፡፡

በየክፍለ ከተማው የተደረገውን ስብሰባ የመሩት ምርጥ የተባሉ ካድሬዎች ቢሆኑም ከመምህራኖቹ የተሰነዘረውን ጥያቄና አስተያየት በአግባቡ ማስተናገድ ተስኖዋቸው ሲሳደቡና ሲያስፈራሩ እንደዋሉም ተጋልጦዋል፡፡

ካድሬዎቹ በውስጣችሁ ያሉትን የትምህርት ጠላት የሆኑትን መምህራኖች መንጥራችሁ አውጡና አጋልጡ እያሉ ሲደነፉ የነበረ ሲሆን መምህራኑ በበኩሉ የትምህርት ጥራቱ ገዳይ ፖሊሲው ነው ሲሉ ምላሽ ከመስጠታቸውም በተጨማሪ በስርዓቱ ውስጥ ሙስና ዋና መገለጫው ሆኖ......የአንድ ወገን የበላይነት ተንሰራፍቶ.....አድልኦና ማግለሉ ተባብሶ ......መልካም አስተዳደር ደብዛው ጠፍቶ......ዲሞክራሲ በጨለመበት ሁኔታ ችግሮቻችሁን ሁሉ መምህራኑ ላይ ለመጣል የምታደርጉት ሩጫ የማይሆንና ሊሳካ የማይችል ከመሆኑም በተጨማሪ ተዓማኒነት የጎደለው ነው ሲሉ ሲሞግቱ እንደዋሉ ታውቆዋል፡፡

ስብሰባው ስምምነት ላይ ሳይደረስ በንትርክ ተጀምሮ በንትርክ መጠናቀቁን የገለፀው የደረሰን ዘገባ በየክፍለ ከተማው ተመድበው የነበሩት ካድሬዎች በቀጥታ ከኩማ ደመቅሳ ጋር የሚገናኙ እንደሆኑም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

በሌላ ዜና በአሁኑ ሰዓት የታሰሩ ጋዜጠኞች ከቤተሰቦቻቸው እና ከህግ ባለሙያዎች ጋር እንዳይገናኙ ተከልክለው ቤተሰቦቻቸው በጭንቀት ላይ እንደሚገኙ የቅርብ ዘመዶቻቸው እየገለፁ ናቸው፡፡

በተለይ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ በተያዘ ዕለት የባለቤቱን መኪና ይዞ የነበረ ሲሆን በወቅቱ መኪናዋን የማዕከላዊ ምርመራ ፖሊሶች አብረው ያሰሩዋት በመሆኑ እስከ ዛሬ ድረስ ያልተለቀቀች መሆኑም ታውቆዋል::

ንብረትነቱ የእስክንድር ባለቤት የሰርካለም ፋሲል መሆኑን ሊብሬና ማስረጃዎችዋን ይዛ ብታቀርብም እስኪጣራ ድረስ አንሰጥም ሲሉ የማዕከላዊ ምርመራ ፖሊሶች የከለከሉዋት ሲሆን እስከ ዛሬ ድረስ ባለቤትዋንም እንዳላገኘችው ገልፃለች::

የማዕከላዊ ምርመራ ውስጥ አዋቂ ምንጮች እንዳሉት ከሆነ ደግሞ በቅርቡ የተያዙት እስረኞች ላይ አሰቃቂ ግፍ እየተፈጸመባቸው እንደሚገኙና ሌሊት ሌሊት ድንገት ለየብቻ እያወጡ ብርድ እና ውርጭ እንዲፈራረቅባቸው እያደረጉዋቸው እንደሆነም አጋልጠዋል:: በዚህ የተነሳ ብዙዎቹ በብርድ በሽታ ተጠቅተው ለከፋ ህመም መዳረጋቸውን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

የታሰሩ ጋዜጠኞች እንዲጎበኙ ዓለም አቀፍ ተቃውሞ ሲበረታበት የጋዜጠኞች ፌዴሬሽን (አይ ኤፍ ጄ) ልዑካን ቡድን እንዲጎበኛቸው የፈቀደ ቢሆንም እራሱ ባደራጀው የብሄራዊ ጋዜጠኞች ማህበር የተሰኘው ለወያኔ አዳሪ የሆነው ማህበር አመራሮች በምስጢር ካሜራ ጉብኝቱ እንዲቀረፅ ለማድረግና ፕሮፓጋንዳ ሊሰሩ መዘጋጀታቸውን እነዚሁ የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል::

በመጨረሻም የስልጣን ዘመናቸው ሊጠናቀቅ 15 ቀናት ብቻ የቀራቸው ፕሬዝዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስ በክብር እንግድነት በተገኙበት የተከበረው የባንዲራ ቀን በፌዴራል ፖሊስ እና በደህንነት ወከባ ታጅቦ ማለፉ ተጋለጠ::

ህዝብ በኑሮ ውድነት እና በችግር ውስጥ ተነክሮ መውጫ አጥቶ ባለበት በዚህ ወቅት እስከ ዛሬ ጨርቅ እያሉ ሲያንቁዋሽሹ የነበረውን ባንዲራ በየዓመቱ እንዲከበር ብለው ዘንድሮም ከ15 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ አድርገው የባንዲራ ቀን አከበርን ማለታቸው ተጋለጠ::

ህዝቡን የስንግ ይዘው ለህዳሴው ግድብ አዋጡ ተብሎ በግዴታ እያዋጣ በጎን ለባንዲራ ቀን ተብሎ 15 ሚሊዮን ብር ለአባሎቻቸው አበል እና ለውስኪ ከህዝብ ካዝና ወጪ እንደተደረገም ታውቆዋል::

የባንዲራ ቀን በአዲስ አበባ ስታዲየም በተከበረበት ወቅት የወያኔ አባሎች ከየቀበሌው እና ከየመስሪያ ቤቱ ተመርጠው የመጡ ሲሆን አስቀድሞ ውሎ አበል የተከፈላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ መጉዋጉዋዣ መኪኖችም በኪራይ የቀረቡላቸው መሆኑ ታውቆዋል::

ስታዲየም ዙሪያ የነበሩ የንግድ ቦታዎችም ለአንድ ቀን እንዳይሰሩ ተከልክለው ይዋሉ ተብሎ ቢታዘዝም ባለ ንግድ ቦታ ባለቤቶቹ አንድ ቀን ኪሳራ ከሽፈናችሁ ይቻላል ያለ በለዚያ ግን አንዘጋም በማለት ከፌዴራል ፖሊስ ጋር ግጭት ፈጥረው እንደነበር ከአይን እማኞች ገለፃ ለማወቅ ተችሎዋል::

የባንዲራ ቀን ለማክበር ከአንድ ቀን በፊት ስታዲየም ውስጥ እና ዙሪያው በፍተሻ ሲታመስ የዋለ ሲሆን ፍተሻው ሲያልቅም ፌዴራሎች ውስጡ እንዲያድሩና እንዲጠበቅ መደረጉ ስርዓቱ ከፍተኛ ጭንቅ ውስጥ መኖሩን ያመላክታል ሲሉም ድርጊቱን የተከታተሉ ወገኖች ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡